# ክርስቶስን መለማመድ፣
# መደሰት እና መግለጥ
# (4)

## ቁልፍ መግለጫዎች

ክርስቶስ እንደ ያሕዌ እና እንደ ሰው
የእግዚአብሔርን ሕዝብ አቅርቦት እየሰጣቸው፤
እየተንከባከባቸው እና እየሸፈናቸው ያለው ንጉሥ ነው፤
ክርስቶስ ለመምራት ንጉሥ ነው፣
ከነፋስ እንደ መሸሸጊያ፣ ከዐውሎ ነፋስም እንደ መጠጊያ፣
በጥም ቦታም እንደ ወንዝ ፈሳሽ፥ በበረሀም አገር እንደ ትልቅ ድንጋይ ጥላ የሆነ ሰው ነው።

ክርስቶስን እንደ የሕይወት ዛፍ እንበላው ዘንድ፣
በነገር ሁሉ የመጀመሪያውን ስፍራ ልንሰጠው ይገባል፣
ይህም እርሱን በሕይወታችን ውስጥ እንደ ሁሉ ነገር እንድንቆጥረውና እንድንወስደው
በፍቅሩ ግድ በመሰኘት እርሱን በመጀመሪያው ፍቅር መውደድ ነው።

ከበጉ ደም የተነሣ
ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ
ከሳሹን ድል ነሡት፥
ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም።

በመንግሥቱ
ጌታ ለሕዝቡ እንደ ፀሐይ በገሃድ ይገለጣል፣
ከታላቁ መከራ በፊት ግን
ሊነጥቃቸው ለድል ነሺዎቹ እንደ የንጋት ኮከብ
በስውር ይገለጣል።

© 2025 Living Stream Ministry

መልእክት አንድ

## ለኢየሱስ ምስክር የታመነው የእግዚአብሔር ምስክር

ራእ. 1፥1-2፣ 5፣ 9-12፤ 7፥9-17፤ 19፥10

**I. ክርስቶስ የታመነው የእግዚአብሔር ምስክር፤ የእግዚአብሔር ምስክር እና መገለጥ ነው፤ እግዚአብሔርን መግለጡ መመስከሩ ነው—ራእ. 1፥5፤ 3፥14፡-**

ሀ. ክርስቶስ የእግዚአብሔር ምስክር እና መገለጥ ነው፤ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ምስክር እና መገለጥ ናት፤ እንደዚህ፣ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር በክርስቶስ ምስክር እና መገለጥ ርቢ ናት—ራእ. 1፥5።

ለ. ራእይ የተገለጠውን ክርስቶስ እና የኢየሱስ ምስክር የሆነችውን የምትመሰክረውን ቤተ ክርስቲያን ያቀርብልናል፤ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ምስክር ነው፣ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ብዙዎች እንደተካተቱበት የሦስታንዱ አምላክ መገለጥ የኢየሱስ ምስክር፣ የተለቀው ክርስቶስ ናት—ዮሐ. 1፥18፤ 5፥31-37፤ 8፥14፤ ራእ. 1፥2፣ 5፣ 9፤ 19፥10፤ ተዛ. ዘፍ. 1፥26።

**II. የኢየሱስ ምስክር ሰባቱ ወርቃማ መቅረዞች ነው—በባሕርይ ወርቃማ (መለኮታዊ)፣ በጨለማ የሚያበራ እና አንዱ ከአንዱ የሚመሳሰል—ራእ. 1፥1-2፣ 9-12፡-**

ሀ. ወርቃማው መቅረዝ ሦስታንዱን አምላክ ይወክላል፤ አብ እንደ ንጥረነገር በወልድ አካል ለብሷል፣ ወልድ እንደ አካል መልበስ በመንፈስ በኩል ተገልጧል፣ መንፈስ እንደ አብያተ ክርስቲያናት በሙላት እውን ሆኗል፣ ተገልጦማል፤ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ የኢየሱስ ምስክር ናቸው—ዘጸ. 25፥31-40፤ ዘካ. 4፥2-10፤ ራእ. 1፥10-12።

ለ. ወርቃማዎቹን መቅረዞችን እንደ ኢየሱስ ምስክር፣ ብዙዎች እንደተካተቱበት የኢየሱስ መገለጥ (ሐዋ. 9፥4-5፤ 1 ቆሮ. 12፥12) ለመለማመድ እንደ ወንድሞችና በኢየሱስ መከራ፣ በመንግሥቱ እና በትእግሥቱ እንደሚካፈሉ (ራእ. 1፡9-10) የኢየሱስን ማኅተም ለመሸከም (ገላ. 6፡17) የጌታ ኢየሱስን ስም ያለማቋረጥ በመጥራት (1 ቆሮ. 12፥3፣ 13፤ ሮሜ 10፥12-13፤ ሰቆ. 3፥55-56) በኢየሱስ መንፈስ መሞላት አለብን (ሐዋ. 16፡7)።

ሐ. መቅረዝ ለመሥራት ወርቁ መቀጥቀጡ የአማኞችን በክርስቶስ መከራዎች መሳተፍ ያመለክታል፤ በከባቢ ሁኔታችን የሚካሄደው ነገር ሁሉ የተቀጠቀጠውን መቅረዝ ለማፍራት ነው—ዘጸ. 25፥31፤ ቆላ. 1፥24፡-

1. አእምሮአችን እግዚአብሔርን በማወቅ ላይ—ለመንፈስ ውስጣዊ ሥራ እና ለውጫዊው ከባቢ ሁኔታ በመገዛት ላይ—እንዲያተኩር ካደረግን፣ እያንዳንዱ ሁኔታ እርሱን እናውቀው ዘንድ እድል ይሆንልናል—ሆሴ. 6፥1-3፤ ፊልጵ. 3፥10፤ ኤፌ. 6፥20፤ ተዛ. ዘፍ. 41፥42።
2. ሰው በሕይወት ዘመኑ እግዚአብሔርን ካላወቀ፣ ሕይወቱን በሙሉ አባክኗል፤ ጌታ ይበልጥ እናውቀው ዘንድ በሁኔታዎቻችን ሁሉ ውስጥ ማደቡን ለመቀበል ፈቃደኞች ያድርገን—2 ቆሮ. 4፥16-18፤ 12፥7-9፤ ተዛ. ኢሳ. 7፥14-15፤ 2 ቆሮ. 5፥14-15።
3. የጉዳዩ ፍሬ ነገር ሰው በችግሮች እና በፈተናዎች መካከል ጌታን እንደ ታላቁ ብርሃን መገናኘት ወይም አለመገናኘቱ ነው፤ መከራ በሌላ በምንም መንገድ መረዳት የማንችለውን ነገር እንድንረዳ ያስችለናል—1፥8-9፤ ተዛ. ኤፌ. 1፥17፤ ሉቃ. 1፥78-79።

መ. የወርቃማዎቹ መቅረዞች ማብራት ሰዎች ክቡሩ ክርስቶስ እንደ የሰው ልጅ በመካከላቸው የመመላለሱን ራእይ ያዩ ዘንድ ነው፤ ጌታን በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ከዘላለም እስከ ለዘላለም እንደሚኖረው በማወቅ፣ ሁልጊዜም በመንፈሳችን ውስጥ ስላለው የእርሱ መገኘት እርግጠኞች መሆን እንችላለን፤ እርሱ ስለ እኛ ሊያማልድ ዘወትር ይኖራል፤ ስለ እኛ አሁን በእግዚአብሔር ፊት ይቀርባል፤ ፈጽሞ አይጥለንም፣ አይተወንም—ራእ. 1፥12-18፤ 2፥1፤ 2 ጢሞ. 4፥22፤ ዕብ. 7፥25፤ 9፥24፤ ዘኁ. 6፥22-27፤ ዘዳ. 31፥6።

ሠ. የወርቃማዎቹ መቅረዞች ሰባቱ መብራቶች ማብራት፣ እንደ እሳት ነበልባል በሆኑ ሰባት ዓይኖቹ፣ እንደሚያንጸባርቅ ናስ በሆኑ እግሮቹና እንደ ፀሐይ በሚያበራው ፊቱ ጌታ ኢየሱስ በመካከላቸው መመላለሱ፣ ለበለጠ የእረኝነት እንክብካቤው—ማዳኑ፣ መመለሱ፣ ማነቃቃቱ እና መለኮት ማድረጉ—ዕለት ዕለት በየቀን ሕይወታችን እና በቤተ ክርስቲያን ሕይወታችን ይበልጥ የጌታ ማብራት እንደሚያስፈልገን ያመለክታል—ራእ. 1፥14-15፣ 16፤ 4፥5፤ 5፥6፤ ሉቃ. 1፥78-79፤ 2 ቆሮ. 4፥6-7፤ ሚል. 4፥2፤ ምሳ. 4፥18፤ መዝ. 22፤ ርዕስ፤ 80፥1-3፣ 7፣ 15-19።

ረ. አብርሆት በእግዚአብሔር ምህረት ላይ ይመረኮዛል፤ እግዚአብሔር በሚመጣበት እና ምህረት በሚያደርግልን ጊዜ ሁሉ፣ የፊቱ ብርሃን ብርሃናችን፤ መገለጡ ራእያችን፣ መገኘቱ ትርፋችን ነው—ሮሜ 9፥15፤ ሐዋ. 9፥3-4፤ ኢሳ. 50፥10-11፤ ዘኍ. 6፥25-26፦

1. አብርሆት ለመቀበል፣ በመሻታችን ሁሉ ጌታን ብቻ ስንፈልግ ልባችንን በእርሱ ላይ ብቻ የሚያተኩር እንዲሆን በማድረግ የጌታን ማብራት መፈለግ እና መቀበል አለብን—መዝ. 139፥23-24፤ ፊልጵ. 2፥12-16፤ 2 ዜና 12፥14፤ 16፥12፤ 34፥1-3፤ መዝ. 27፥8፤ 73፥25፤ ሉቃ. 11፥33-36።
2. አብርሆት ለመቀበል ራሳችንን ለጌታ መክፈት፤ ልባችንን ወደ እርሱ ማዞር፣ ምንም ሳናስቀር እና ሳንቆጥብ ራሳችንን በፊቱ ማስቀመጥ አለብን፤ ራሳቸውን ለጌታ ዝግ የሚያደርጉ ሰዎች ሌሎች ላይ በመፍረድ እና በመተቸት የተካኑ ናቸው—2 ቆሮ. 3፥16፤ ምሳ. 20፥27፣ ማቴ. 7፥1-5፤ ሉቃ. 6፥36-37፣ 41-42።
3. አብርሆት ለመቀበል፣ ራሳችንን ማስቆም አለብን፤ ይህም ማለት እይታችንን፣ ነገሮችን የምናይበትን መንገድ፣ ስሜቶቻችንን፣ ሃሳቦቻችንን እና አመለካከቶቻችንን ማስቆም ማለት ነው፤ ሙሉ በሙሉ የቆመ ሰው በጌታ ፊት በሚመጣበት ጊዜ፣ የጌታን ቃል ሲቀበል እጅጉን ያልተከፋፈለ ትኩረት ያለው እና ቀላል መሆን ይችላል—10፥38-42፤ ዮሐ. 11፥21-28፤ ኢሳ. 40፥31፤ ማቴ. 5፥3፤ ሉቃ 18፥15-17፤ ኢሳ. 66፥1-2።
4. አብርሆት ለመቀበል፣ በውስጣችን ከሚናገረው የመንፈስ ብርሃን ጋር መከራከር የለብንም፣ በውጭ ከሚናገሩን የመንፈስ አገልጋዮችም ጋር መከራከር የለብንም—ሐዋ. 22፥10፤ መኃ. 5፥4-6፤ 2 ቆሮ. 10፥3-5፤ 11፥2-3፤ ዘኍ. 16፥1-7፣ 31-39፤ 17፥1-8፤ ተዛ. ዘጸ. 33፥11-14።
5. አብርሆት ለመቀበል፣ ያለማቋረጥ በብርሃን መኖር አለብን—ኢሳ. 2፥5፤ 1 ዮሐ. 1፥7፤ ዕብ. 9፥14፤ 10፥22፤ ማቴ. 5፥3፣ 8፣ 14፤ መዝ. 119፥105፤ ራእ. 1፥20፤ መዝ. 36፥8-9።

**III. የኢየሱስ ምስክር፣ ዛሬ መደሰት ከምንችላቸው በሰማያዊ ስፍራ እና በክርስቶስ ውስጥ ካሉት መንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ ጋር የእግዚአብሔርን እንክብካቤ እና የበጉን እረኝነት ለመደሰት ወደ ሰማያት የተነጠቁት በመቅደሱ ውስጥ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ እጅግ ብዙዎቹ ሰዎች፣ በእግዚአብሔር የተዋጁትን ሁሉ ያቀፈ አካል ነው—ራእ. 7፥9-17፤ ኤፌ. 1፥3፤ ገላ. 3፥14፤ ዘፍ. 12፥2፤ ተዛ. ራእ. 21፥3-4፤ 22፥3-5፤ ኢሳ. 49፥10፦**

ሀ. እጅግ ብዙዎቹ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን ክፍል ለመሆን ከሕዝብ፣ ከነገድ፣ ከወገንና ከቋንቋ በበጉ ደም የተዋጁትን ያካትታል—ራእ. 7፥9፤ 5፥9፤ ሮሜ 11፥25፤ ሐዋ. 15፥14፣ 19፤ 1 ቆሮ. 6፥19-20።

ለ. "እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፥ ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ"—ራእ. 7፥14፦

1. በቁጥር 14 ያለው ታላቁ መከራ በእግዚአብሔር የተዋጁት ሕዝብ በዘመናት ሁሉ የተለማመዱትን መከራዎች፣ ስቃዮች፣ ስደቶች እና ጉስቁልናዎች ያመለክታል—ዮሐ. 16፥33።
2. የበጉ ደም ዲያቢሎስ በእኛ ላይ ያለውን ክሶች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ይመልሳል፣ በእርሱም ላይ ድልን ይሰጠናል (ራእ. 12፥11)፤ ለኃጢአታችን እና ለርኩሰታችን ሁሉ የተከፈተው የደም ምንጭ (ዘካ. 13፥1፤ ዮሐ. 19፥34) ከሆነው ከሚቤዠው ክርስቶስ የተነሣ፣ በዚያ ደም ውስጥ መጥለቅ፣ የጥፋተኝነት እድፈቶችን ሁሉ ማስወገድ (ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ #1006፣ ቁጥር 1) እና "ከዓለም እና ከኃጢአት በላይ/ በታደሰ ልብና በነጻ ልብስ/ ክርስቶስ በውስጥ ነግሦ/ በእግዚአብሔር በራሱ ብርሃን ለመመላለስ መነሣት" እንችላለን (ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ #1010፣ ቁጥር 3)።
3. ልብሳችንን ማጠብ በበጉ ደም ማጠብ ምልልሳችንን ንጹሕ አድርጎ መጠበቅ ነው፤ ይህ የሕይወትን ዛፍ ለመደሰትና እንደ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ በረከት ክልል ወደ ሕይወት ከተማ ውስጥ ለመግባት መብት ይሰጠናል—1 ዮሐ. 1፥7፤ ራእ. 22፥14።

ሐ. እነዚያ እጅግ ብዙ ሰዎች በእጆቻቸው የዘንባባ ዝንጣፊዎች ይዘው በዙፋኑ እና በበጉ ፊት ቆመዋል—7፥9፦

1. የዘንባባ ዝንጣፊዎች ስለ ጌታ ያለፍንበትን መከራ ማሸነፋችንን ያመለክታሉ፤ የዘንባባ ዛፎች በመረስረስ የሚገኝ እርካታ ምልክትም ናቸው—ቁ. 14፤ ተዛ. ዮሐ. 12፥13፤ ዘጸ. 15፥27።
2. የእግዚአብሔር መቅደስ በሆነው በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ፣ እንደ ዘላለማዊው የዳስ በዓል እርሱን ለመደሰትና እንደ የዘንባባ ዛፍ በሕይወት ለማበብ ቀንና ሌሊት እናገለግለዋለን—ራእ. 7፥15፤ 3፥12፤ ዘሌ. 23፥40፤ ነህ. 8፥15፤ መዝ. 92፥12-13፤ ዮሐ. 7፥2፣ 37-39፤ ሮሜ 1፥9፤ ቆላ. 2፥19።
3. ዛሬ በጊዜ ውስጥ ያለን አገልግሎት በዘላለም ውስጥ ለሚኖረን አገልግሎት ዝግጅት ነው፤ በጊዜ ውስጥ የእግዚአብሔር ብቸኛው ግብ ዕለት ዕለት ራሱን ወደ ውስጣችን ማደል ነው፤ እግዚአብሔር ወደ ውስጣችን ሲመጣ እና ከውስጣችን ሲወጣ፣ ያ አገልግሎት ነው—ማቴ. 25፥19-23፤ ዮሐ. 7፥37-39።

መ. ከእንግዲህ አንራብም ወይም አንጠማም—ራእ. 7፥16፦

1. መራብ እና መጠማት ገና ያልረካ ተስፋ ያለው መሆን ነው፤ ክርስቶስ ወደ እርሱ ውስጥ የሚያምኑ ሁሉ እንደሚረኩ እና እንደሚያረካቸው ሕይወት እንደሚቀበሉት ቃል ገብቷል—ዮሐ. 6፥35።
2. እግዚአብሔር መንፈስን በመንፈሳችን መገናኘት ከሕያዉ ውኃ መጠጣት ነው፣ ከሕያዉ ውኃ መጠጣት ደግሞ እውነተኛ አምልኮ ለእግዚአብሔር ማቅረብ ነው—4፥13-14፤ 23-24።

ሠ. የሚወርደው ፀሐይ እና የሚያቃጥለው ትኩሳት አይመታንም—ራእ. 7፥16፦

1. በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው በጉ-አምላክ እኛን በመጸለል በእኛ ላይ ያድራል—ቁ. 15፤ 2 ቆሮ. 12፥9።
2. በእግዚአብሔር መጸለል ሥር ያለ አንድ የሕይወት ዓይነት አለ—በእግዚአብሔር ውስጥ የተሰወረ ሕይወት ነው—መዝ. 36፥7-9፤ ኤፌ. 6፥17፤ መዝ. 91፥1፤ 17፥8፤ 57፥1፤ ሩት 2፥12።
3. ክርስቶስ እንደ ያሕዌ እና እንደ ሰው የእግዚአብሔርን ሕዝብ አቅርቦት እየሰጣቸው፤ እየተንከባከባቸው እና እየሸፈናቸው ያለው ንጉሥ ነው፤ ለመምራት ንጉሥ ነው፣ ከነፋስ እንደ መሸሸጊያ ከዐውሎ ነፋስም እንደ መጠጊያ፣ በጥም ቦታም እንደ ወንዝ ፈሳሽ፥ በበረሀም አገር እንደ ትልቅ ድንጋይ ጥላ የሆነ ሰው ነው—ኢሳ. 32፥1-2።

ረ. በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ በእረኝነት ይንከባከበናል፣ ወደ ሕይወት ውኃ ምንጮችም ይመራናል—ራእ. 7፥17፦

1. የእረኝነት እንክብካቤ መመገብን ያካትታል፤ በክርስቶስ እረኝነት ሥር “ምንም አላጣም”—መዝ. 23፥1።
2. ራሳችንን ማሻሻል ፈጽሞ አንችልም፣ ሁልጊዜም እንዲመግበን እረኛ ያስፈልገናል፤ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እና ለእግዚአብሔር ቤት በዙፋኑ ላይ ያለው የእግዚአብሔር በግ በመሆኑ ባለው ልምምድ በጎችን ይመግባል—ቁ. 2-6፤ ራእ. 22፥1።

ሰ. እንባዎችን ሁሉ ከዓይናችን ያብሳል—7፥17፦

1. በዚህ ዘመን እንባዎች የማይቀሩ ናቸው፣ ነገር ግን እንባዎቻችን በእግዚአብሔር ጠርሙስ ውስጥ ይቀመጣሉ፣ በመጽሐፉም ይጻፋሉ—ዕብ. 5፥7፤ ሐዋ. 20፥19፣ 31፤ መዝ. 56፥8፤ ተዛ. ሚል. 3፥16።
2. ለእርካታችን በጉ በሕይወት ውሃዎች አቅርቦት ስለሚሰጠን፣ የእንባዎች ውኃ ይታበሳል—ኤር. 9፥1፤ 2፥13፤ ተዛ. 15፥16፤ ሰቆ. 3፥21-25፣ 55-56።
3. የኀዘን ቀናት እና የኀዘን ነገሮች ስለማይዘልቁ እግዚአብሔር ይመስገን፤ ዓለም እያለፈ ነው፣ እኛም የዘላለም ሕይወት ጥቅል ድምር፣ አዲሲቷን ኢየሩሳሌም እስከንሆን ድረስ የሚፈሰውን ሥስታንዱን አምላክ ለመጠጣት ተባርከናል—ዮሐ. 4፥14።

© 2025 Living Stream Ministry